በውነቱ ይህ ቀን በየስታዮ ፈተኞቹው የበሩ በጣም በርካት ሰዎ የተገኘበት ዓውም የማይረሳ ቀን ነበር። አል-ቃዲ ሙሐሙዲን ያደረገው ትግባቡ አር-ረውድተይን በሚል ርዕስ ከተማፈው መፅሃፍ በሁለቱ ተፅ ውስጥ ሰፍር ይገኛልና የንግግሩን የተወሰነ ክፍል እንደሚከተለው አትርበነዋል።-

ሪ ነ ሠይ! የመጨረሻ ግብ ከሆነውና ከሁሉም በላይ ከሆነው አላጋ ዘንድ መልካም ብሥራት ሙየተላችኋልና እንኳን ደስ አላችሁ። ለመቶ ዓመት አካባቢ በመሸሪከት መጫፍ ውስጥ ከቆየች በኋላ ይህ ያልተቋረጠ ትግልና ጥረት በአንተ እንዲሳካ (የእየሩሳሌም ነፃ መውጣት) አላህ አስቻላችሁ። በተን እንድታዘዱ አላህ ረዳችሁ። ስሙን እያነሳችሁ እንድታወድሰት ፈቀደላችሁ። ጣሪያና ግድግዳውን የሞሉትን የሸርክ ሥዕሎችና ምልክቶች በሙሉ ጠራርጋችሁና አንዕታችሁ ዘተትዋ ምሰሶዎች እንድትተካቸው ረዳችሁ። ወደተመሰረተበት ዓላማው እንድትመልሱት እደረጋችሁ። ዋንኛም የአባታችሁ ኢብራሒም መኖሪያ ነበር። ነቢዩ ሙሐመድ (የአላህ ሰላምና ዐጋ በእርሳቸው ላይ ይሁን) ወደ ሰማይ ያረገበት ቦታ ነበር። አሰላም እንደ አዲስ ከመምጣቱ በፊት የመኖሪያ ቲዘላችሁ ነበር። የነቢያትና የአላህ መልዕክተኞች መቀመጫ ነበር። የቅን ሰዎች ሁሉ መጻረሻ ነበር። ይህ ቦታ የአሰላም ምንጭ ወህይ የወረደበት ቦታ፣ ሐራምና ሐላል የተነሰጠበት ቦታ፣ የትንሳኤ ቀን ሰዎች የሚሰበሰቡበት ቦታ(አንዳ አል-መሕሸር)፣ በተቀደሰው ቁርአን የተጠቀሰ ቅዱስ ቦታ ነው። ነቢዩ ሙሐመድ (የአላህ ሰላምና ዐጋ በእርሳቸው ላይ ይሁን) መላእክዎችን በሰላት የመሩት እዚህ መስጂድ ውስጥ ነው። ይህ ቦታ አላህ አገልጋዩን፣ መልዕክተኞቹን፣ ሰመርሃምና ከእርሱ ሰሆነው መንፈስ (ያ መልዕክተኛውና ነቢዩ በማንረግ ወጻከበረው መንፈስ) የተከበረ ቃሉን የላከበት ቦታ ነው። አላህ በተከበረው ቃሉ እንዲህ ይላል።-

﴿ لَّن يَسْتَنكِفَ ٱلْمَسِيحُ أَن يَكُونَ عَبْدًا لِّلَّهِ وَلَا ٱلْمَلَٰٓئِكَةُ ٱلْمُقَرَّبُونَ ۚ وَمَن يَسْتَنكِفْ عَنْ عِبَادَتِهِۦ وَيَسْتَكْبِرْ فَسَيَحْشُرُهُمْ إِلَيْهِ جَمِيعًا ﴿١٧٢﴾ ﴾ النساء: ١٧٢

"አልመሲሕ (ኒሳ) ለአላህ ባሪያ ከመኾን ፈጽሞ አይጠየፍም፤ ቀራቢዎች የንጎት መላእክትም፤ (አይጠየፉም)፤እርሱን ከመግዛት የሚጠየፍና የሚኮራም ሰው፤ (አላህ) ሁሉንም ወደ እርሱ በርግጥ ይሰበስባቸዋል።" (አን-ኒሳእ፡ 172)

እንዲሀም ብሏል፡-

﴿ لَّقَدْ كَفَرَ ٱلَّذِينَ قَالُوٓا۟ إِنَّ ٱللَّهَ هُوَ ٱلْمَسِيحُ ٱبْنُ مَرْيَمَ ۖ قُلْ فَمَن يَمْلِكُ مِنَ ٱللَّهِ شَيْـًٔا إِنْ أَرَادَ أَن يُهْلِكَ ٱلْمَسِيحَ ٱبْنَ مَرْيَمَ وَأُمَّهُۥ وَمَن فِى ٱلْأَرْضِ جَمِيعًا ۗ وَلِلَّهِ مُلْكُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ وَمَا بَيْنَهُمَا ۚ يَخْلُقُ مَا يَشَآءُ ۚ وَٱللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَىْءٍ قَدِيرٌ ﴿١٧﴾ ﴾ المائدة: ١٧

"እነዚያ «አላህ እርሱ የመርየም ልጅ አልመሲሕ ነው» ያሉ በእርግጥ ካዱ። «የመርየምን ልጅ አልመሲሕን፣ እናቱንም፣ በምድር ያለንም ሁሉ ለማጥፋት ቢሻ፣ ከአላህ ማዳንን የሚችል ማነው?» በላቸው። የሰማያትና የምድር፣ የመካከላቸውም ንግሥና የአላህ ብቻ ነው፤ የሚሻውን ይፈጥራል። አላህም በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው።" (አል-ማኢዳህ፡ 17)

የመጀመሪያው ቲበላ ክሳዕባ ቀጥሎ የተነፐረ ሁለተኛው መስጅድ እና በደረጃም ክሳዕባና ከነቢዩ መስጂድ ቀጥሎ የሚገኝ መስጅድ ይኸው የምንገኝበት መስጅድ ነው። ከሁለቱ የተከበሩ መስጂዶች ቀጥሎ ሰዎች ጉዟቸውን ሸክፈው በመትጋት መድረሱ ለንዘለት የሚገባ መስጂድም ነው። አላህ ከህዝቦች ሁሉ በላይ ባይመርጣችሁ ኑሮ ማንም የማይደርስበትንና ለቀናቀናችሁ የማይችለውን ዕድል አይሰጣችሁም ነበር። በነቢዩ (የአላህ ሰላምና ዐጋ በእርሳቸው ላይ ይሁን) ጊዜ በድር ላይ እንደተሳተፉት፤ ከአበበክር ጋር እንደወጉት፤ በዑመር ጊዜ ሠፊ ግዛት እንዳቀናጉትና ነፃ እንዳወጡት፤ ልክ እንደ ዑስማን መታደሮችና የሃሰትን አንገት እንደቆረጡት የዓሊ ሠራዊት

ዓይነት ተዓምር የሚሰራ ሠራዊት በመስጠት ባርኳችኃል። በአልቃዲሲያ፣ በየርሙክና በኸይበር ጦርነቶች የተጀመረውን ደግማችሁ በስኬት አጠናቅቻኃል። እንደ ዝለድ ኢብኑ ወሊድ በጅግንነት ተዋድቃችኃል። ትግላችሁን፣ ጥረታችሁን፣ ያፈሰላችሁትን ደም፣ የከፈላችሁትን መስዋዕትነት አላህ ይቀበላችሁ፣ ፍሁም የተሳካላችሁ ሰዎች መነሪያ ቤት የሆነችውን ጀነት ይሸልማችሁ። የዚህን ክስተት ግዘፈት በሚገባ መረዳት አለባችሁ፣ ግዚህ ግዙፍ ክስተት ባለቤት ስላደረጋችሁም ተገቢውን ምስጋና ለአላህ ማድረስ አለባችሁ።"

ከዚህ ትልቅ ድል በኋላ ገጣሚዎች፣ ምሁራን፣ ወሐፊዎች እ ታሪክ ዘጋቢዎች ቀስ እያሉ መደ እየሩሳሌም ጎረፉ። ወሐፊዎ በብዕራቸው፣ ገጣሚዎች በግጥማቸው ሰላሑዲንን አሞገሱት። ለምሳ ያህል ገጣሚና ታላቁ ሊቅ አቡልሐሰን ኢብን ዓሊ የማክብሉትን የግጥ ስንኞች ቋጥሮ ነበር።

አላህ ለዚህ ንጉስ ሠማያዊ ሠራዊት አድሉታል
የሚጠራጠር ካለ የቁድስ ነፃነት ማስረጃ ሁኖ ቀርቦለታል
ምንጊዜም ጠንካራ ሁነው የኖሩት ቂሳራዊያን
ይኸው መዳፉ ውስጥ ትንሽ ሁነው ተቀምጠዋል
እየሩሳሌም ከወገኖቿ ጋር መቶ ዓመት አለተሰች
በደንታቢስ ሙስሊም መሪዎች ጆሮ ተነፍጋ ስለኖረች
ይኸው ዛሬ ሰላሑዲን የሁሉንም ጥሪ መለሰ
በአላህ ፍቃድ ዕንባቸውን ሊያብስ ደረሰ
ነገ የሁሉም ሰው የሥራ መዕለፍ ይዘጋል
የሰላሑዲን መዕላፍ ግን ተከፍቶ ይቀራል
ምክንያቱም የትየለሌ መልካም ሥራዎች ሠርቷል

አል-ጁወይኒይኒ በሚል ስም የሚታወቁት መሐመድ ኢብን አሰድ አል-ሐሰቢ በበኩላቸው የሚከተለውን ግጥም ዕፈው ነበር።

የየሩሳሌምን ነፃ መውጣት ማመን አትዮጵል

የመስቀልኞችን መንከታከት ማመን ተስኖኛል

ግን ዕውነት ሁኗል

ሁኖ የማያውቀውን ንጉሳቸው ክንሪችን ታስሯል

እስር ውስጥ የኖሩት ሊቨንት የሩሳሌም

የፍርዱ ቀን ዐታ ነፃ ወጥተዋል

ዑመር እንዳደረገው ቱድስን ያነፃው

ዐስማን እንዳደረገው ኢስላምን የረጨኸው

የነቢዩ ትንቢት እንዲፈፀም የረዳህው

የየሩሳሌም ነፃ አውጪ ዩሱፍ አሲዲት ብየሃለው

ስላሑዲን የመስቀል ወራሪዎችን የያዘበት ሁኔታ

በስላሑዲን እና በመስቀል ወራሪዎች መካከል በተደረገው ስምምነት መሠረት ፍራንክች በአርባ ቀናት ውስጥ እየሩሳሌምን ለቀው እንዲወጡ የሚያስገድድ፣ እንዲሁም በሚወጡበት ጊዜ እያንዳንዱ ሰው በነፍስ ወከፍ የተጣለበትን ክፍያ በመክፈል ነፃነቱን እንዲገዛ፣ ለወንዶች አሥር ዲናር፣ ለሴቶች አምስት ዲናር፣ ለልጆች ሁለት ዲናር መተመኑን ይህን መክፈል የማይችሉ ሰዎች ግን ምርኮኛ ሁነው እንዲቀሩ የሚያስገድድ አንቀፅ ስምምነቱ ሚከተቱን ቀደም ብለን መጥቀሳችን ይታወሳል።

ይሁን እንጂ የመስቀል ወራሪዎች በወረሩት ህዝብ ላይ ለዘመናት ሲፈፅሙ ለኖሩት ኢሳትዛዊ እና በሞካኔ የተሞላ ተግባራቸው ሰላሑዲን ምላሽ ሞካኔ አልነበረም። ይልቁኑ ጨቋኝና አምባገነን ንጉሶችና ቤተሠቦቻቸውን በእንከብከቤ ነበር የያዛቸው። እግረ መንገዱን አስልምና የእዘነት፣ የርሕራሔና የፍትር ኃይማኖት መሆኑን ራሳቸው ለአሥርት ዓመታት ለፈፀሙት ግፍ ሰይፍ መምዘዝ ሲገባው፣ እነሱ ሲያደርጉ እንደኖሩት ማዋረድና ማንገላታት ሲችል፣ ሰላሑዲን ግን በኢስላም አስተምህሮ የተቀረፀው ስብዕናው ይህን እንዲያደርግ

አልፈቀደለትምና በእንዘክዘቤ አስተናገዳቸው። በዚያውም የኢስላም ሰብዓዊ ገፅታ አስገነዘቧቸው።

ለመሆኑ ሰላሑዲን የተጠየቁትን ገንዘብ መክፈል አቅቷቸዉ ምርኮኛ ሁነው የቀሩትን መስተለሻችስ እንዴት ነበር የያዛቸው?

በጣም ብዙ ፍራንክች በዕድሜ የገፉ ወላጆቻቸውንና ዘመዶቻቸውን በጀርባዎቻቸው ተሸክመው ይዝዙ ነበር። ሰላሑዲን ይህን ሁኔታቸውን ቁም ማየት አልቻለም። በጣም ተረበሸ። በጣም አዘነ። ወዲያውኑ ገንዘብ እንዲሰጣቸው ትዕዛዝ አስተላለፈ። ዕቃዎቻቸውን የሚሸከሙላቸውና የጉዞ ሸኮማቸውን የሚያቀሉላቸው እንስሳዎች እንዲተርፉላቸው አደረገ።

ከውስጣቸው አንዲት ሃብታም ሴት ነበረች። ይህች ሴት የቤዛንታይኑ ንጉስ ሚስት ነበረች። ዓለማዊነትን ትታ በምንኩስና መኖርን የመረጠች ሴት ነበረች። የአርሷን መንገድ የተከተሉ በርካታ ሴቶችም በዙሪያዋ ይገኙ ነበር። ሰላሑዲን ለዚህች ሴትና አብረዋት ለሚገኙ ሌሎች ሴቶች የተለየ እንክዘክዘቤ እንዲደረግላቸው አድርጎ ነበር።

ንግስት ሳያቢል ተክታዮቿን ይዛ መሐዲ እንደምትረዳ በመግለፅ ሰላሑዲን እንዲሔዱ እንዲፈቅድላቸው ስትጠይቀው በትህትና ነበር የፈቀደላት። ያለችበት ሁኔታ ልዙን ስለነካው ናዝሉስ ውስኖ እስረኛ ሁኖ ወደ ተቀመጠው ባሏ መሳጭት። ከጎኑ እንድትቀመጥም ፈቀደላት። ልጆቻቸውን በክንዶቻቸው ሃዲቀፉ ብዙ ሴቶች ተከትለዋት ነበርና ሱልጣኑ ካለበት ቦታ ሲደርስ፦ "ንጉስ ሆይ! እንደሚያዩን አሁን ለተን መሐዳችን ነው፤ እርስዎ ዘንድ የሚገኙት አስረኞች ሚስቶቻቸው፤ እናቶቻቸው፤ ወይም ሴት ልጆቻቸው ነን፤ ይህችን ከተማ እና ተንከባከቢዎቻችን እንዲሁም ጠባቂዎቻችን የነበሩ አስረኛ ወገኖቻችንን ስለመፈታታቸው ተለያይን መሐዳችን ነው። ንጉስ ሆይ! በፈለጉ ሊገድሏቸው ይችላሉ ነገር ግን ከዚያ በኋላ እኛ ሕያውት አይኖረንም። ምህረት ካደረጉላቸው ግን ያለተንከባከቢዎቻችን እና ያለጠባቂዎቻችን መኖር አንችልምና ስቃያችንን የሚተነስ፤ ሽኮማችንን የሚያቀል ትልቅ ውለታ እንደዋሉልን እንቆጥረዋለን።" በማለት ምህረት ጠየቁት።

አሳዘኑት። እምቢ ማለት አልቻሉም። ስለዚህ መጣቸን ለእናታቸው፣ ላጉን ለሚስቶቻቸው እንዲሁም አባቶችን ለልጆቻቸው ሲል ነፃ ለቀቀላቸው። የቀሩትን አስረኛ ወሮቻቸውን በርህራሄና በዕዝነት እንደሚያገለግሏቸው ቃል ገባላቸው።

አስቲቨንሰን እንዳስተመጠው "በጣም ብዙ ሰዎችን ለመከፈል የተስማሙትን ገንዘብ ሳይተበል ነበር ነፃ የሰተታቸው። ሱልጣኑ ለአነስ ልንክላን እና ችግረኛ ሰዎች ያለ ክፍያ እንዲሌዱ እንድ ቀን ሰጥቷቸው ነበር" በማለት አርኖልድ መዘገቡን ጥል ያንግርናል። ከዚህ ሁሉ በተጨማሪ ቂሰችና ሊሎች ብዙ ሃብት አከማችተው የነበሩ ሰዎች የሚፈልጉትን ያህል እንዲወስዱ ፈቅዶላቸው ነበር። ተሸከሙው መውሳት ያልቻሉትን ንብረት ደግሞ ሙስሊሞች በመግዛት እንዲተዘረቸው አድርጎ ነበር።

ማሊክ አል-አዲል ለሰባት ሺህ ደካማና ችግረኛ ሰዎች ክፍያው እንዲቀርላቸው መንድሙን ሰላሉዲንን ጠየቁ። ሰላሉዲን እሥር ሺህ ሰዎች ከክፍያ ነፃ እንዲሆኑ አደረገ።

ሰላሉዲን ፍራንክኮችን የያዘበት ሁኔታ እርስ በርሳቸው ከነበራቸው ግንኙነት የተሻለ፣ በወረራ ኒሸንፈው ሲዝ ሙስሊሞችን ካደረገቸው ጋር ፍፁም የማይመሳሰል ነበር።

እየሩሳሌምን ለቀው የሌዱ በርካታ ቁጥር ያላቸው ክርስቲያኖች ከክርስቲያናዊ አንጾቲያ ሲደርሱ ከልዕላኑ የጠበቁቸው ግፍተራ እንጂ ሌላ እንዳልነበር፣ መሌኛ አዮተው መደ ሙስሊም አገሮች ሲሌዱ ግን በቀላሉ እንደተቀበሏቸው ሚል የተባለ እንግሊዛዊ የታሪክ ሰው ሌልዕል ዓሊ አመጌው ዮት ነበር።

ልዑል ዓሊ እንዲህ ብሏል፦

ከእየሩሳሌም ተባርረው የወጡ ሰዎች ክርስቲያን መንድሞቻቸው ዘንድ ስለንጠማቸው ሁኔታ። ጎሪያ ውስጥ በርካቱ ተቀቡ፣ በችጋር ታሹ፣ ሰብዓዊ ክብር ተነፈጋቸው። ትሪፖሊ በረን ከረችመችባቸው፣ እናቶች ልጆቻቸውን ወደ ባህር ለመወርወር ተገደዱ። እናኪህም